የሰ/መ/ቁ. 48628

ግንቦት 5 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- አቶ በርሄ ሐጐስ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የስር ከሣሽ /ያሁን የሰበር አመልካች/ በስር ተከሣሽ /በሰበር ተጠሪ/ ያቀረበው ክስ ተከሣሹ ንብረትነቱ የራሱ በሆነው ኮድ3-29644 አይሱዙ የጭነት መኪና 56 ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ጭኖ ከጨርጨር ወደ መቀሌ ከተማ በ26/4/2001 ዓ.ም ምሽት 3፡30 ሲጓዝ እጅ ከፍንጅ በመያዙ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 60/89 በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/1/ ተላልፎ በመገኘቱ ተከሷል የሚል ነው፡፡

ተከሣሹም ፍ/ቤት ቀርቦ የእምነት ክህደት ቃሉ ሲጠየቅ ወንጀሉን አለመፈጸሙንና ጥፋተኛ አለመሆኑን ክዶ በመከራከሩ የስር የትግራይ ክልል ደቡብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ከቀረቡት የግራ ቀኙ ማስረጃዎች አንጻር ከመረመረ በኋላ ከሣሹ ጠቅሶ ክስ ያቀረበበትን የወንጀል አንቀጽ 64/1/ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 113/2/ መሠረት ለውጦ በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 74 ስር ጥፋተኛ ነው በማለት ተከሣሹ በ3 ዓመት ቀላል እስራትና በ5000 ብር መቀጮ እንዲቀጣ ፣ የተያዘው 56 ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ለመንግስት ገቢ እንዲሆንና መኪናው ለተከሣሽ እንዲመለስ በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የትግራይ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በበኩሉ የይግባኝ ባዩን /የስር ከሣሽን/ ይግባኝ በመሠረዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195/1/ ይግባኝ ባዩን አሰናብቷል፡፡

በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ ቅር የተሰኘው የአሁኑ አመልካችም ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 60/89 ያሻሻለው አዋጅ ቁጥር 365/95 አንቀጽ 64/4/ ተጠሪው በራሱ መኪና በህግ የተከለከለውን 56 ቦንዳ ጭኖ በመገኘቱ ክስ ተመስርቶበትና በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ተጠቅሶ ክስ ከቀረበበት የህግ አንቀጽ መንፈስ ወጪ መኪናው ለተጠሪ ይመለስ ተብሎ የተወሰነው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የተፈጸመው የህግ ስህተት ታርሞ መኪናው ለመንግስት ገቢ እንዲደረግ እንዲወሰን ጠይቋል፡፡

ለሰበር ቅሬታው ተጠሪው በሰጠው መልስ አመልካች በ24/6/2001 ዓ.ም ለስር ትግራይ ክልል ደቡብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ወንጀሉ ብቻ የሚመለከት እንጂ አሁን ቅሬታ የቀረበበት መኪና ይወረስልኝ በሚል አይደለም፡፡ ስለሆነም በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ሲል ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተመለከተው አጥሮ የቀረበ ሲሆን እኛም በተጠሪ አሽከርካሪነት 56 ቦንዳ ልባሽ ጨርቅ ጭኖ የተያዘው መኪና ለመንግስት ገቢ ሊሆን ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ጠቅሶ ክስ ያቀረበበትን አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4/ ከግራ ቀኙ ማስረጃዎች አንጻር ሲመረመር ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የለውም በሚል በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 74 ስር ጥፋተኛ ነው ብሏል፡፡ በዚህ አንቀጽ ጥፋተኛ የተደረገ ሰው ደግሞ የተያዘበት ዕቃ መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዕቃው ላይ ሊከፍል ከሚገባው ጠቅላላ የቀረጥና የታክስ ሂሣብ በማያንስ የገንዘብ መቀጮና ከሶስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል፡፡

በዚህ በተያዘው ጉዳይ ግን የስር ፍ/ቤት እንዳረጋገጠው ያሁኑ የሰበር ተጠሪ ንብረትነቱ የራሱ በሆነው አይሱዙ የጭነት መኪና የተጠቀሰውን የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭኖ ሲጓዝ እጅ ከፍንጅ ተይዟል፡፡ በዚህ የወንጀል ድርጊትም በአዋጁ የማጓጓዝ ሀላፊነት የሚያስከትለውን ግዴታ በመጣሱ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያለው እንደ ስር ፍ/ቤቶች አተረጓጐም አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 74 ሣይሆን የተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 64/4/ ነው፡፡ የተጠሪው ድርጊት በአንቀጽ 64/4/ የሚሸፈን ከሆነ ደግሞ የሚወረሰው በኮንትሮባንድ የተያዘ ዕቃ ብቻ ሣይሆን የዕቃው ማጓጓዣ /መኪና/ ጭምር ነው፡፡

በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች አመልካችን ጠቅሶ ክስ ያቀረበበትን የህግ ቁጥር ያለአግባብ በመለወጥ ጥፋተኛ ነው በማለት የቅጣት ውሣኔ ያስተላለፋበት የህግ ቁጥር የማጓጓዣ ሀላፊነት ግዴታ ጥሶ ለተገኘው ለመጓጓዣው ባለቤት ተፈጻሚነት የሌለው በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የስር የትግራይ ክልል ደቡብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 10/12117 በቀን 24/10/2001 በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የትግራይ ክልል ጠ/ፍ/ቤት የወንጀል ችሎት በመ/ቁ 33108 በቀን 06/12/2001 ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽለዋል፡፡
2. የሰበር ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4/ ስር ጥፋተኛ ነው ብለን ወስነናል፡፡ ቅጣትን በሚመለከት የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በ3 ዓመት ቀላል እስራትና በ5000 /አምስት ሺ.ህ/ መቀጮ ተጠሪው እንዲቀጣ የወሰነው በአግባቡ በመሆኑ ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ተጠሪው ጥፋተኛ የተደረገበት አዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 64/4/ የኮንትሮባንድ ዕቃ የጫነው ማጓጓዣ ጭምር እንዲወረስ የሚደነግግ በመሆኑ በተጠሪ አሽከርካሪነት የተያዘው የተጠሪ ኮድ 3-29644 አይሱዙ የጭነት መኪና ተወርሶ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ወስነናል፡፡
4. መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

እ.ከ                                                                 የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት